# 7. በጥንታዊቷ መርጡለማርያም ገዳም ዙሪያ የሚነገሩ አፈ-ታሪኮች የገዳሚን ህልውና ከማስጠበቅ አንጻር ያላቸው ፋይዳ

በሔለን አላምረው እና በድርቧ ደበበ

## አጠቃሎ

ይህ ጥናት በመርጡለማርያም ገዳም ዙሪያ የሚነገሩ አፈ-ታሪኮች የገዳሚን ህልውና በመጠበቅ በኩል ያላቸው ፋይዳ ምን እንደሆነ መመርመርና መተንተን ዋና አላማው ሲሆን ይህን አላማ ለማሳካትም በቃለ-መጠይቅና በተተኳሪ የቡድን ውይይት መረጃ ተሰብስቧል፡፡ የተሰበሰበው መረጃም ተግባራዊ/ፋይዳዊ ንድፈ ሀሳብን በመጠቀም በገላጭ፣ተንታኝ ስልት የተተነተነ ሲሆን አፈ-ታሪኮቹ የገዳሚን ህልውና ከመጠበቅ አንጻር የሚጫወቱትን ሚና ለማወቅ አስችሏል፡፡ የጥናቱ ውጤት እንደሚያሳየው በመርጡለማርያም ገዳም ዙሪያ የሚነገሩ አፈ-ታሪኮችን ታሪክ ማህበረሰቡ አምኖ እንዲቀበል እግዚአብሄር፣ማርያም፣የኢትዮጵያ የቀድሞ ነገስታት በአካባቢው የሚታወቁ የቦታ ስያሜዎች እንደሚጠቀሱ ተስተውሏል፡፡ እንዲሁም በታሪካዊቷ መርጡለ ማርያም ገዳም ዙሪያ የተነገሩና የሚነገሩ አፈ ታሪኮች በገዳሚ እና በማህበረሰቡ አባላት ላይ የተፈፀሙ ጥቃቶች በድንግል ማርያም ልዩ ተዓምር መክሸፉን በማሳየት ማህበረሰቡ በገዳሚ ዙሪያ ለሚገጥሙ ጥቃቶች ድንግል ማርያምን ተስፋ አድርጎ ፊት ለፊት ሊጋፈጥ እንደሚገባ ያነሳሳሉ፡፡ገዳሚን ሊያጠቋት የሚሞክሩ ጠላቶችም እንደማይሳካላቸውና እንደሚዋረዱ ያስጠነቅቅበታል፡፡ በተጨማሪ በገዳሚ የሚፈፀሙ ዘረፋዎችን የማህበረሰቡ አባላት ሊመክቱ እንደሚገባ፤ምዕመናን ለአባቶች ሊታዘዙ እንደሚገባ፤የጸበሏን ፈዋሽነትና ታሪካዊነቷን በማጉላት ቦታዋ እንድትተከልና እንድትከበር የማድረግ ህልውናዋ ተጠብቆ በዘላቂነት እንዲኖር የማድረግ ፋይዳ አፈ - ታሪኮቹ እንዳላቸው ከጥናቱ ለመረዳት ተችሏል፡፡ በመሆኑም አፈ ታሪኮች በአሁኑ ሰአት እንደተራ ነገር የሚቆጠሩበት ሁኔታ ስለሚታይ በተለያዩ ገዳማትና አድባራት ቀርስን ከመጠበቅ አንጻር የሚጫወቱት ሚና ከፍተኛ በመሆኑ በማሰባሰብና በማደራጀት ረገድ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡

**ቁልፍ ቃላት:- ገዳማትና አድባራት፣ተዓምር፣አፈ-ታሪክ**

## 1. መግቢያ

### 1.1.የጥናቱ ዳራ

አፈ-ታሪክ በአንድ አካባቢ በተከሰተ እውነተኛ ያለፈ ነጠላ ታሪክ ላይ የተወሰኑ የፈጠራ ታሪኮች ታክለውበት ታሪኩን ማን ፈጸመው?፣የት ተፈጸመ?፣መቼ ተፈጸመ?፣ለምን ተፈጸመ?፣እንዴት ተፈጸመ? ለሚሉት ጥያቄዎች መልስ የሚሰጥና በዝርው የትረካ ቅርጽ ከትውልድ ትውልድ በቃል የሚተላለፍ የስነ-ቃል ዘርፍ ነው፡፡ (ዘሪሁን 2000 ዓ.ም.)

በአፈ-ታሪክ ስለነገስታት፣ታዋቂ ግለሰቦች፣ተፈጥሯዊ ክስተቶች ለምሳሌ፡-በአንድ ወቅት የተከሰተ የጎርፍ አደጋ፣የመሬት መንቀጥቀጥ በአንድ አካባቢ ስላሉ ተራሮች፣ሀይቆች፣ሜዳዎች፣ ስለሐይማኖታዊ ስፍራዎች፣ስለ ከተሞች አቆራቆር ታሪክ ይነገራል (ሰሎሞን 2007 ዓ.ም.) ስለዚህ አፈ-ታሪክ በተለያዩ ጉዳዮች ዙሪያ የሚነገር እንደመሆኑ አይነቶቹ ብዙ ናቸው፡፡

የተለያዩ ምሁራን የአፈ-ታሪክ አይነቶችን በተለያየ መንገድ የሚከፍሏቸው ሲሆን ‹‹የአፈ-ታሪክ አይነቶች እርስ በርስ የሚቀራረብ ባህርያት ስላላቸው አንዱን ከሌላው በቀላሉ መለየት አስቸጋሪ ነው፡፡››(ሰለሞን 2007 ዓ.ም፣ 96) ምሁራን አፈ-ታሪኮችን የሚመድቡባቸው መስፈርቶችን አስመልክቶ አፈ-ታሪኮች ያላቸውን ይዘት፣ጠቀሜታ፣መገኛ ስፍራና የስርጭት መጠን መሰረት እንደሚያደርጉ አብራርቶታል፡፡

በዘርፉ ምሁራን ተደጋግመው የሚነሱ የአፈ-ታሪክ አይነቶች ታሪካዊ (Historical)፣የታጋይ (Heroic)፣ ሮማንቲክ ወይም ሚቲክ (Romantic or Mythic)፣ሐይማኖታዊ (Religious)፣ ሚቶሎጂያዊ (Mythological)፣ገለጻዊ (Etiological)፣አካባቢያዊ(Local)፣ተንቀሳቃሽ (Migratory)፣ ዘመናዊ (Contemporary)፣የከተማ (Urban)፣ሜሞሬት (Memorate)፣ፋቡሌት(Fabulate)፣ ልዕለ ተፈጥሯዊ (Supernatural) ናቸው፡፡ (ሰለሞን 2007 ዓ ም.፣ፈቃደ 1991 ዓ.ም፣ Degh in Dorson 1972፣ OKopeho 1992) በዚህ ጥናት በመርጡለ ማርያም ገድም ዙሪያ የሚነገሩ እና የገዳሚን ህልውና ለመጠበቅ ያላቸው ፋይዳ ምን እንደሚመስል ለመመርመር ሲባል የተሰበሰቡት አፈ-ታሪኮች ምደባን ስንመለከት ታሪካዊ አፈ-ታሪክ (Historical Legend) እና ሮማንቲክ ወይም ሚቲክ አፈ-ታሪክ (Romantic or Mythic Legend) ውስጥ የሚመደቡ ሆነው አግኝተናቸዋል፡፡

#### 1.1.1. ታሪካዊ አፈ-ታሪክ

ይህ የአፈ-ታሪክ አይነት በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ ሊታወሱ ስለሚችሉ የቅርብና የቅርብ ያለፈ ጊዜ ድርጊቶች፣ሁኔታዎችና ግለሰቦች የሚተርክ ሆኖ የአፈ-ታሪኩ እውነተኛ መልክ ጎልቶ

እንዲወጣ ተደርጎ የሚቀርብ ነው። አድማጮች ስለሚተረተው ነገር ለመተቸት የሚያስችል መረጃ ስለሚኖራቸው ተራቹ የሚጨምራቸው የፈጠራ ታሪኮች የተገደቡ ናቸው ።
(ፈቃደ 1991 ዓ.ም.)

ታሪካዊ አፈ-ታሪክ በሶስት አይነት መንገዶች ሊከፈል ይችላል የመጀመሪያው በአንድ አገር ወይም አካባቢ ስለሚታወቁ ጀግኖች የሚተርክ ሲሆን ሁለተኛው የአንድን ማህበረሰብ ህይወት ያወከ አጋጣሚ እንደ ማህበረሰቡን ያጠቁ ባዕዳን ታሪክ፣የጨካኝ መሪዎች ታሪክ ይመለከታል። ሶስተኛው ደግሞ ስለተለያዩ ቦታዎች፣ተራሮች፣ወንዞች ስያሜ አሰጣጥ የሚተርኩ ናቸው። (Degh in Dorson 1972)

### 1.1.2.ሮማንቲክ ወይም ሚቲክ አፈ-ታሪክ

በዚህ አፈ-ታሪክ ስር የሚነሱ ድርጊቶችም ሆኑ የግለሰቦች የጥንት የሚባሉ ናቸው። በመሆኑም የጥንት ስለሆኑና የመረጃ ጥያቄ የሚያነሳ ስለሌለ ተራቹ ታሪኩን ከራሱ ፍላጎት አንጻር ሊያጋንነውና የማይታመኑ ነጥቦችን ሊያነሳበት ይችላል። በአገራችን፡-ስለንግስት ሳባና ሰለሞን፣ ስለዮዲት፣ስለኢዛና፣ስለካሌብ ወዘተ.የሚተረኩ ትረካዎች በዚህ ስር ሊካተቱ ይችላሉ።
(ፈቃደ 1991 ዓ.ም.)

የፎክሎር ባለሙያዎች እንደሚሉት በቃላዊ ታሪክ ውስጥ የሚገለጹት ድርጊቶች የአድማጩን አዕምሮየሚይዙ፣በአዕምሮው ለሚፈጠሩ ጥያቄዎች መልስ የሚሰጡ እና በእምነት(በሐይማኖት) ከሚቀበላቸው ነገሮች ጋር የሚያያዙ ከሆኑ ማህበረሰቡ የሚፈልግበትን ህላፊነት እንዲወጣ ያስችሉታል። ይህም አፈ-ታሪክን የመሰሉ ፎክሎሮች ያላቸውን ፋይዳ የሚያሳይ ነው። (*An Encyclopidia of Beliefs, Customs, Tales, music and Art.1997)*

አፈ-ታሪኮች አንድ ማህበረሰብ በአካባቢው የሚገኙ ቅርሶችን እንዲያውቅ፣ እንዲጠብቅና የኔነት ስሜት እንዲሰማው የሚያነሳሱት ከሆነ በአገራችን ጥንታዊ የሆኑ ገዳማትን ህልውና ለማስጠበቅም የሚጫወቱት ሚና ከፍተኛ እንደሆነ የዚህ ጥናት አቅራቢዎች እናምናለን። በመሆኑም በዚህ ጥናት በጥንታዊቷ መርጡለማርያም ገዳም ዙሪያ የሚነገሩ አፈ-ታሪኮች የገዳሟን ህልውና በመጠበቅ በኩል ያላቸው ፋይዳ ምን እንደሆነ ለመመርመር ተነሳሳን ::

ጥንታዊቷ መርጡለ ማርያም ገዳም በምስራቅ ጎጃም ዞን የምትገኝና ‹‹የአባይን ወንዝ ተከትለው ወደ ኢትዮጵያ የገቡ የኩሽ ነገዶች ይኖሩባቸው ከነበሩ ጥንታውያን ቦታዎች አንዷ ናት›› አባ ኃይለ ኢየሱስ(2010፣8)። የኩሽ ነገዶች የቦታ አቀማመጧ፣ የአካባቢው ልምላሜና የአየር ንብረቷ ለኑሮ ምቹ መሆኑን በማየት ‹‹ሀገረ እግዚአብሔር›› በማለት የሰየሟት ሲሆን በቦታው

ላይ ነገደ ካም ወይም የኩሽ ልጆች በሕገ ልቡና እግዚአብሔርን እያመለኩ እንደ አባታቸው አዳም መስዋዕት እየሰው ከ4,500 ዓመተ ዓለም እስከ 2,800 ለ1700 ዓመት እንደኖሩባት አባ ኃይለ ኢየሱስ ያስረዳሉ፡፡

በገዳሚ ታሪክ ላይ አባ ኃይለ ኢየሱስ ገ/ማርያም 2010 ዓ.ም፣ምትኩ ደምሴ 1995 ዓ.ም፣ ሀብታሙ መንግሥቴ 1998 ዓ/ም እና በ Paul B. Henze 1919 በስፋት ጽፈዋል፡፡ በእነዚህ አጥኝዎች የገዳሚ ታሪክ፣ ቅርስ እና በገዳሚ ላይ የተፈፀሙ ጥቃቶችና ጥቃት አድራሽ ግለሰቦች በስፋት ተብራርተዋል፡፡ ይህ ጥናት ግን የገዳሚን ህልውና ለማስጠበቅ የተገለገሉባቸውና እየተገለገሉባቸው የሚገኙ አፈ-ታሪኮችን የሚመረምር በመሆኑ በሌሎቹ ጥናቶች የታየውን ክፍተት ይሞላል፡፡ አፈ-ታሪኮች የሥነ ቃል ዘርፎች ከመሆናቸው ባሻገር የማኅበረሰቡን አመለካከትና እውቀት ለመረዳት የሚያስችሉ በመሆናቸው የቤተክርስቲያን ታሪኳን፣ ቅርሷን፣ ምዕመናን እንዴት እንደምትጠብቅበት ለመረዳት ያስችላል፡፡ በመሆኑም ይህ ጥናት የአፈ-ታሪኮቹን ፋይዳ መመርመር ላይ ያተኩራል፡፡

## 1.2. የጥናቱ መነሻ ምክንያት

ጥናቱን ለማድረግ ካነሳሱ ምክንያቶች አንዱ ፍላጎት መኖር ነው፡፡ ፍላጎት ያሳደሩ ምክንያቶች ሐዲስ አለማየሁ በ2012 ዓ/ም ባዘጋጀው ጉዞ ላይ መሳተፍና በግል ገዳሚን መጎብኘት ነው፡፡ በዚህም ለመረዳት እንደተቻለው ታሪኩን ለማጥናት የተለያዩ ሰዎች በግልና በቡድን እንደሚመጡና እንደሚመራመሩ ነው፡፡ የዚህ ጥናት አድራጊዎችም በድጋሚ ወደ ቦታው በመሄድና በመመልከት፣ በመጠየቅ ከታሪኩ ይልቅ የገዳሚን ህልውና ለመጠበቅ እስከአሁን ለመዝለቅ ያስቻለው ምክንያት ያልተጠና በመሆኑ ተረኮችን በመሰብሰብ ጥናቱን ለማድረግ ተነሳሳን፡፡ በተጨማሪ በገዳሚ ዙሪያ የተሰሩ የተለያዩ ድርሳናትን በማንበብ ለመረዳት እንደተቻለው አፈ-ታሪኮችን በመሰብሰብ የገዳሚን ህልውና ከማስጠበቅ አንጻር ያላቸው ፋይዳ ያልተጠና በመሆኑ ጥናቱን ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

## 1.3. የምርምር ጥያቄዎች

ይህ ጥናት የሚከተሉትን ጥያቄዎች ይመልሳል፡-

1. በገዳሚ ዙሪያ የሚነገሩ አፈ ታሪኮች ያለፈውንም ሆነ የአሁኑ ትውልድ ገዳሚን እንዲወድ፣ እንዲንከባከብ እና እንዲጠብቅ የሚያደርጉት በአፈ- ታሪኮቹ ውስጥ ምን ምን ነገሮች ስለሚጠቀሱ ነው?

2. በገዳሚ ዙሪያ የሚነገሩ አፈ-ታሪኮች የገዳሚን ህልውና ከመጠበቅ አንጻር የሚጫወቱት ሚና ምንድን ነው?

## 1.4.የጥናቱ ዓላማ

የጥናቱ ዋና አላማ ከገዳሚ ጋር ተያይዘው የሚነገሩ አፈ-ታሪኮች የገዳሚን ህልውና በማስጠበቅ ያላቸው ፋይዳ ምን እንደሆነ መመርመርና መተንተን ነው፡፡ የሚከተሉትን ዝርዝር አላማዎችም ይዟል፡፡

- የገዳሚን ህልውና ለማስጠበቅ የተገለገሉባቸውና እየተገለገሉባቸው የሚገኙ አፈ- ታሪኮችን መሰብሰብ፣
- በገዳሚ ዙሪያ የሚነገሩ አፈ-ታሪኮች ያለፈውንም ሆነ የአሁኑ ትውልድ ገዳሚን እንዲወድ፣ እንዲንከባከብ እና እንዲጠብቅ የሚያደርጉት በአፈ- ታሪኮቹ ውስጥ ምን ምን ነገሮች ስለሚጠቀሱ እንደሆነ መግለጽ
- የአፈ-ታሪኮችን ፋይዳ መተንተንና መተርጎም ናቸው፡፡

## 1.5.የጥናቱ ጠቀሜታ

ይህ ጥናት የሚከተሉት ጠቀሜታዎች አሉት ፡-

- ከገዳሚ ጋር ተያይዘው የሚነገሩ አፈ-ታሪኮች የገዳሚን ህልውና ከመጠበቅ አንጻር ያላቸውን ፋይዳ የሚያሳይ በመሆኑ የነበረውንና ያለውን አመለካከት ለመረዳት ይጠቅማል፡፡
- በፎክሎር፣ በአንትሮፖሎጂ፣ በታሪክና መሰል መስኮች ምርምር ለሚያደርጉ የመረጃ ምንጭ ሆኖ ያገለግላል፡፡
- ይህን ጥናት ለሚያነቡ ግለሰቦችም ሆነ በባህልና ቱሪዝም ቢሮዎች ምዕመኑ ገዳሚን እንዲወድና እንዲጠብቅ ከሚያደርጉት ነገሮች መካከል አፈ - ታሪኮች የሚጫወቱት ሚና ከፍተኛ እንደሆነ ያስገነዝባል፤
- በቃል የሚነገሩ ሀብቶችን መሰነድ እንደሚገባ ይጠቁማል፡፡

### 1.6.የጥናቱ ገደብ

አፈ-ታሪኮች ስለተለያዩ ታሪካዊና ሐይማኖታዊ ቦታዎችና ድርጊቶች ቢነገሩም ይህ ጥናት ግን በምስራቅ ጎጃም ከሚገኙ ጥንታዊ ታሪክ ካላቸው የመጀመሪያ በሆነችው በመርጡለ ማርያም ገዳም ዙሪያ ከሚነገሩ ሥነ- ቃሎች ውስጥ በዝርው የሚቀርቡትን አፈ-ታሪኮችን መሰብሰብና ፋይዳቸውን መተንተን ላይ ብቻ የተወሰነ ነው፡፡

## 2. የጥናቱ ዘዴ

በዚህ ርዕስ ስር መረጃ መሰብሰቢያና መተንተኛ ዘዴዎች ቀርበዋል፡፡

### 2.1. መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ

በዚህ ጥናት አስፈላጊ የሆኑ አፈ-ታሪኮችን ለመሰብሰብ ቃለ መጠይቅና ተተኳሪ የቡድን ውይይትን ተጠቅመናል፡፡

#### 2.1.1. ቃለ-መጠይቅ

ቃለ መጠይቅ በገዳሚ ዙሪያ የሚነገሩ አፈ-ታሪኮችን ለመሰብሰብ ያገለገለ ሲሆን በአላማ ተኮር ዘዴ ሃያ አምስት ሰዎች ተመርጠው ዝግና ክፍት ጥያቄዎችን በመጠቀም ሃያ አፈ-ታሪኮች ተሰብስበዋል፡፡

#### 2.1.2. ተተኳሪ የቡድን ውይይት

ስምንት ስምንት አባላትን ያቀፈ ሁለት ተተኳሪ የቡድን ውይይት የተደረገ ሲሆን በቃለ-መጠይቅ የተሰበሰቡት አፈ ታሪኮች ዙሪያ ግልጽ ሊሆኑ የሚገባቸውን መረጃዎች ለማጥራት ተጠቅመንበታል፡፡ በተጨማሪ የተሰበሰቡ አፈ-ታሪኮች ፋዳቸው ምን እንደሆነ እንዲገልፁ በማድረግ ከማህበረሰቡ አተያይ አንፃር መረጃውን ለማደራጀት አገልግሎት ላይ ውሏል፡፡

### 2.2. የመረጃ መተንተኛ ዘዴ

ጥናቱ አይነታዊ ጥናት ሲሆን የተሰበሰቡት አፈ-ታሪኮች በገላጭ ተንታኝ መንገድ ተገልፀዋል፡፡ እንዲሁም የዚህ ጥናት መተንተኛ የሆነው ተግባራዊ /ፋይዳዊ ንድፈ ሃሳብ ነው፡፡ ተግባራዊ ንድፈ ሃሳብ ጥቅም ላይ ከሚውልባቸው መስኮች አንዱ ሀይማኖታዊ ፎክሎር ነው

(Dorson,1972፡25)፡፡ በአንድ ማህበረሰብ ወይም ፎክ ቡድን ውስጥ ያሉ የተለያዩ ሎሮች ለፎክ ቡድኑ (ለማህበረሰቡ) የሚሰጡትን ተግባር/ጥቅም ማሳየት ላይ ትኩረት ያደርጋል፡፡

በርካታ የፎክሎር ምሁራን የሚስማሙባቸውን አጠቃላይ የፎክሎር ተግባሮች ፈቃደ በስድስት ይከፍሏቸዋል፡፡ ይኸውም የመግለጥ ተግባር፣ የማጠንከር - የመትከል ተግባር፣ የማምለጥ ተግባር ፣ የማስተማር ተግባር ፣ የመግታት-የመቆጣጠር ተግባርና ፖለቲካዊ ተግባር በማለት ነው(1991፣16-22)፡፡ የፎክሎር ዘርፍ በሆነው ስነ-ቃል አንድ ማህበረሰብ በታሪክ የሚታወቁ ሰዎችን የጀግንነት፣ የቆራጥነት፣ የጽኑ እምነት፣ የታጋይነት ወዘተ.ትዕምርቶች በመተረክና በማስረጽ አርዓያነታቸውን ዘላለማዊ ለማድረግ ይሞክራል፡፡ አንዳንዶቹንም የፈጸሟቸው ተግባራት እና ገድላቸው በተለያዩ ሁኔታዎች በማህበረሰቡ ዘንድ እንዲዘከርና እንዲከበር በማድረግ የእነሱ ተግባር በማህበረሰቡ ዘንድ ለጣቂነት እንዲኖረው በማድረግ የማጠንከር፣ የመትከል ተግባሩን እንደሚጫወት ያስረዳሉ(ፈቃደ 1991፣ 18)፡፡

Sims እና Stephens (2005 : 179) ደግሞ ተግባራዊ ንድፈ ሀሳብን በፎክሎር መጠቀምን ለመጀመሪያ ጊዜ ያስተዋወቀው (Bascom,1965) መሆኑን ገልጸው የፎክሎር ተግባርን ጠቅልሎ በአራት ክፍሎች (ማስተማር፣ ከእለት የእለት ህይወት ማምለጥ ፣ ባህላዊ እሴቶችን መጠበቅ እና በማህበረሰቡ ዘንድ ተቀባይነት ያላቸውን ልማዶችን መጠበቅ) በሚል ማስቀመጡ ትክክል እንዳልሆነ በመተቸት እያንዳንዱ ማህበረሰብ አንድን የፎክሎር ቅንጣት እንደየ አውዱ የሚከውንበት ምክንያት እንደሚለያይና የእያንዳንዱ ቅንጣት ተግባር ምን እንደሆነ ለማወቅ የተከወነበትን አውድና ምክንያት መመርመር እንደሚያስፈልግ ይገልጻሉ፡፡

በአጠቃላይ በዚህ ጥናትም የተግባራዊ ንድፈ ሀሳብ ጽንሰ ሀሳብ በመጠቀም በመርጡ ለማርያም ገዳም ዙሪያ የሚነገሩ አፈ-ታሪኮችን ከሚቀርቡበት አውድ እና ምክንያት አንጻር በመፈተሽ የማጠንከር፣ የመትከል፣ የመጠበቅና የማስተማር ሚናን(ተግባርን) እንዴት እንደሚጫወቱ ለመመርመር አመችቶናል፡፡ እንዲሁም አፈ ታሪኮቹ ማህበረሰቡ የሚነገረውን ታሪክ አምኖ እንዲቀበል ምን ምን ነገሮችን ይጠቅሳሉ ወይም ይጠቀማሉ፤ በአፈ-ታሪኩ ተፈጸሙ ተብለው የሚነገሩት ድርጊቶች ማህበረሰቡ(አማኙ) ቤተ-ክርስትያኗን የመጠበቅ ሃላፊነት እንዲሰማው ከማድረግ አንጻር ምን ሚና ይጫወታሉ? የሚሉትን ጥያቄዎች መሰረት አድርገን የአፈ-ታሪኮቹን ፋይዳ ለመፈተሽ አስችሎናል::

### 2.3. የመረጃ አሰባሰብ ስነ-ምግባር

በዚህ ጥናት በመርጡለማርያም ገዳም ዙሪያ የሚነገሩ አፈ-ታሪኮችን የሰበሰብነው በቦታው ተገኝተን፣ ለመረጃ ሰጭዎች ለምንና ከየት እንደመጣን አስረድተን መረጃ ለመስጠት ፈቃደኝነታቸውን ካገኘን በኋላ ሲሆን ፍላጎታቸው ካልሆነ በጥናታችን ስማቸውን እንደማንጠቅስም አስረድተናቸዋል፡፡

## 3. የመረጃዎች ትንተናና ማብራሪያ

በዚህ ክፍል በታሪካዊቷ መርጡለ ማርያም ገዳም ዙሪያ የሚነገሩ አፈ-ታሪኮች ከተግባራዊ ንድፈ ሀሳብ አንጻር ተተንትነው ቀርበዋል፡፡ ጥናቱ አይነታዊ ጥናት እንደመሆኑ የተሰበሰቡ መረጃዎች በገላጭ ተንታኝ መንገድ ተገልፀዋል፡፡ የጥናቱ ትኩረት የስነ - ቃል ዘርፍ ከሆኑትና በዝርው ከሚቀርቡት መካከል አፈ ታሪክ ላይ ነው፡፡ የአፈ-ታሪክ ጥናት ትኩረትን በተመለከተ ዘሪሁን አስፋው እንደሚከተለው ይገልፁታል፤

> *የአፈ-ታሪክ አላማ አንዳንድ አሳሳቢ ጥያቄዎችን ለመመለስ ነው፡፡ በታሪክ የነበረው ሰው ያከናወናቸውን ተግባራት መልካምነት ወይም መጥፎነት ለማረጋገጥ ይነገራል፡፡ በታሪክ የተፈጸመ አንድ ድርጊት እንዴት ሊፈጸም ቻለ ፣ ለምን ተፈጸመ፣ የሚሉ ጥያቄዎች ሲነሱ በአፈ-ታሪክ መልስ ይሰጣል* (ዘሪሁን 1992፡31-32)፡፡

በዚህ ጥናት የተሰበሰቡ አፈ-ታሪኮችም መርጡለ ማርያም ገዳም ስትቆረቆር ጀምሮ እዚህ እስከደረሰችበት ጊዜ ድረስ የቆረቆሯት አካላት እና የሐይማኖት አባቶች ያሳለፏቸውን ጥሩም ሆነ መጥፎ አጋጣሚዎች በመግለጽ እንዴት እንደተወጡት በማሳየት ለተተኪው ትውልድ ያስተምራሉ፡፡

ቀጥሎ በገዳሟ ዙሪያ የሚነገሩ አፈ ታሪኮች ያለፈውንም ሆነ የአሁኑ ትውልድ ገዳሟን እንዲወድ፣ እንዲንከባከብ እና እንዲጠብቅ የሚያደርጉት በአፈ- ታሪኮቹ ውስጥ ምን ምን ነገሮች ስለሚጠቀሱ ነው?፣ በገዳሟ ዙሪያ የሚነገሩ አፈ-ታሪኮችስ የገዳሟን ህልውና ከመጠበቅ አንጻር የሚጫወቱት ሚና ምንድን ነው? የሚሉትን የጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄዎች መሰረት አድርገን የአፈ-ታሪኮቹን ፋይዳ እንመለከታለን፡፡

### 3.1. ማህበረሰቡ የሚነገረውን ነገር አምኖ እንዲቀበል በአፈ-ታሪኮች የሚጠቀሱ ነገሮችና ፋይዳቸው

በዚህ ጥናት የሰበሰብናቸው በመርጡለ ማርያም ገዳም ዙሪያ የሚነገሩ አፈ-ታሪኮችን ታሪክ ማህበረሰቡ አምኖ እንዲቀበለው እግዚአብሄር፣ማርያም፣ የኢትዮጵያ የቀድሞ ነገስታት (ቀዳማዊ ምኒሊክ፣ አብረሃ ወ አጽብሃ፣አጼ ገላውዲዎስ) እና በአካባቢው የሚታወቁ የቦታ ስያሜዎች የሚጠቀሱ ሲሆን እነዚህ አካላት በየደረጃቸው በማህበረሰቡ ዘንድ ያላቸው እውቅና፣ክብርና ተቀባይነት ከፍ ያለ ነው፡፡ በመሆኑም እነሱ የተጠቀሱበትና ተሳትፈውበት የተቆረቆረ ቤተ-ክርስትያን እና የተፈጸመ ታሪክ ማህበረሰቡ ሲነገረው ቅርሱን እንዲጠብቅ የማበረታታት ጉልበቱ ከፍተኛ ነው፡፡ ለምሳሌ፡- ቀዳማዊ ምኒልክ ፣ንጉስ ሰለሞን እና ገዳሟ በምትገኝበት ምስራቅ ጎጅም ዞን የሚታወቁ የቦታ ስያሜዎች የተጠቀሱበትን አፈ-ታሪክ እንመልከት፡፡

> *ቀዳማዊ ምኒልክም ኢትዮጵያ እንደደረሰ መንግስትን ከእናቱ ከማክዳ ተቀብሎ በኢትዮጵያ ነገሰ፡፡ አብረውት የመጡ ነገደ እስራኤልንም በየሙያቸው ደልድሎ በየ ግዛት ሀገሩ ላከ፡፡ ሲደለድልም ፈረሰኞችን በአስተዳደር፣ ሌዋውያን ካህናት እና ጠበብት እስራኤልን ደግሞ ለመኖር የሚያስችለውን መሳሪያ ከማምረት ባሻገር ምኩራብ ኦሪትን እንዲሰሩና እግዚአብሔርን እንዲያገለግሉ አደረገ፡፡ በጊዜው ጎጃምን እንዲያስተዳድር ከጭፍሮችና ከሌዋውያን ካህናት ጋር ወደ ጎጃም የተላከው አለቃ ኤፍሬም ነበር፡፡ ኤፍሬም ከሰሜን ኢትዮጵያ ወደ ጎጃም ምድር እንደገባ ርዕሰ ከተማውን ነገደ ካም ቀደም ሰፍረውበት በነበረችው ሀገረ ሰላም አደረገ፡፡ አብረውት የመጡ ባለሟሎቹንም በመላው ጎጃም እየደለደለ ላከ፡፡ ለምሳሌም፡-- በርዕሰ ከተማዋ ዙሪያ ከደለደላቸው ብንጠቅስ እለ ብሴ እግዚአብሔር በአሁኑ አጠራር-- እነብሴ፣ እለ እሴይ ሶስተኛ በአሁኑ አጠራር--ሲሶ እነሴ፣ እለ እሴይ ሁለተኛ በዛሬው አጠራር -- ሁለት እጁ እነሴ ተብለው የሚጠሩትን በአካባቢው ድልድሎ ስራውን ሲሰራ ኖረ፡፡ ይህ አካባቢ እስከ አሁን የሚጠራው ለአገልግሎት ተመድበውበት በነበሩት ነገዶች ስም ሆኖ--- ጠበብት እስራኤልና ሌዋውያን ደግሞ የኦሪቱን ወግና ስርዓት ጠብቀው በሀገረ ሰላም ቤተ ምኩራብ እንዲሰሩ አደረገ (ምትኩ፣1995 ዓ/ም)፡፡*

የዚህን አፈ-ታሪክ ፋይዳ በምናይበት ጊዜ የተጠቀሱት ወረዳዎች በምስራቅ ጎጃም ዞን የሚገኙና የራሱ የመርጡለ ማርያምና በመርጡለ ማርያም ከተማ አካባቢ የሚገኙ ወረዳዎች ስያሜ መሆናቸውን ማህበረሰቡ ጠንቅቆ ያውቃል፡፡ በአፈ-ታሪኩ ውስጥ እነዚህ ስያሜዎች መጠቀሳቸው የአፈ-ታሪኩን አድማጭ/አንባቢ ትኩረት ይስባል፡፡ በተጨማሪ ስያሜዎቹ ለየት ያሉ ናቸው፡፡ ማህበረሰቡ እነዚህ ወረዳዎች ለምን እንደዚህ ተባሉ ብሎ በሚጠይቅበት ጊዜ ከላይ የቀረበው ታሪክ ምክንያቱን ስለሚነግረው ለጥያቄው መልስ ከማግኘቱ በተጨማሪ ስያሜዎቹን እንዲቀበል ያደርገዋል፡፡ እንደዚሁም አፈ-ታሪኩ የቤተ-ምኩራቡን ታሪክ በማቅረብ አሁን መርጡለ ማርያም ያለችበት ቦታ እግዚአብሔር ከጥንት ጀምሮ ማለትም ከክርስቶስ

ልደት በፊትም ይመሰገንበት እንደነበር በማሳየት የቦታው ታሪካዊነት ጎልቶ እንዲወጣ በማድረግ በኢትዮጵያ በቅርብ ጊዜ ከተሰሩት ቤተ-ክርስትያኖች በተለየ ሁኔታ ታሪካዊነቷን ለማጉላት ያስችላል፡፡

ከስያሜው ባሻገር የኦሪት መስዋእት የተሰዋባት መሆኗ መተረኩ ገዳሚ ከክርስቶስ ልደት በፊት የተመሰረተች ታሪካዊት መሆኗን ይጠቁማል፤ በመሆኑም ማህበረሰቡ ይህን አፈ ታሪክ ሲሰማ የቀዳሚነት ሚና የሚገልጽ አፈ ታሪክ በመሆኑ በደስታ ተቀብሎ እንዲጠብቅ የማነሳሳት ተግባር አለው፡፡

ከዚሁ ጋር በተያያዘ የሐዲስ ኪዳኑን ቤተ-ክርስትያን አሰራር ታሪክ የሚተርከውን አፈ-ታሪክ ብናይ ቤተ-ክርስትያኑ በ330 ዎቹ ገደማ የኢትዮጵያ ነገስታት በነበሩ አብርሃ እና አጽበሃ እና በወዳጃቸው አቡነ ሰላማ ጥረት መሰራቱን ይነግረናል፡፡

> *አብርሃና አጽበሃ ከሰላማ ከሳቴ ብርሃን ጋር በመሆን የአባይን ወንዝ ተሻግረው ጎጃም ጽርሃ አርያም አንባ እንደደረሱ የአንባውን አቀማመጥና የቤተ-ምኩራቡን ውበት ዞረው ተመልክተው ሲጨርሱ ቤተ-መቅደሱ ቦታውን እንደያዘ ለታሪክ መዘክር እንዲቆይ ወሰኑ፡፡ስለዚህም ጽርሃ አርያም አንባ በስተምስራቅ አሻጋሪ አብራሂ ኮረብታ ላይ የሐዲሱን ቤተ-ክርስትያን ለመስራት መሰረት ጀመሩ ፡፡ መሰረቱ ተጀምሮ እንዳለ ግን መሬቱ በሚቆፈርበት ጊዜ እንደ እሳት ትንታ ብልጭ እያለ አልቆፈርም በማለቱ ቤተ-ክርስትያኑ በዚያ ቦታ እንዲሰራ እግዚአብሄር አለመፍቀዱን ቅዱሳን ነገስታቱና አቡነ ሰላማ ስለተረዱ ፈቃደ እግዚአብሔርን ለመጠየቅ ከሚከተሉት ቦታዎች ሱባኤ ገቡ፡፡---ለሶስት እለታት በየባእታቸው ጸንተው እንዳሉ በሶስተኛው ሌሊት ሁሉንም እግዚአብሄር በራእይ አነጋገራቸው ራእዩም አስራ ሁለት በሮች ያሏት አንድ አምደ ብርሃን የቤተ-መቅደሱን መሰረት ከጀመሩበት አብርሂ ኮረብ ተነስታ እያበራች በኦሪቱ ቤተ-መቅደስ ጋር ተያይዛ ከጽርሃ አርያም አንባ ላይ ታየቻቸው፡፡ ---በራእያቸው መሰረትም ጽርሃ አርያም አንባ ላይ ከኦሪቱ ቤተ መቅደስ ጋር አያይዘው ከግራና ከቀኝ ወደ ፊት አስፋፍተው መሰረቱን በመጣል የህንፃ ቤተ-ክርስትያኑን ስራ ጀመሩ፡፡ ስራውም በመንፈስ ቅዱስ እርዳታ ቀን ተሰርቶ የዋለው በሶስት እጥፍ እያደገ አድሮ በመገኘቱ አስራ ሁለት ቤተ-መቅደስ ሆኖ በጥራትና በፍጥነት ተሰርቶ አለቀ* (ቃ.መ. ቢያድግልኝ፣2012 ዓ/ም)፡፡

ይህ አፈ-ታሪክ ለቤተ-ክርስትያኗ ህልውና ምን ፋይዳ አለው በምንልበት ጊዜ በሁለት መንገድ ማየት ይቻላል፡፡ የመጀመሪያው ማህበረሰቡ አሁን በተጨባጭ ቤተ-ክርስትያኗ ቅጥር ግቢ ውስጥ ፈራርሶ የሚገኘውን በጣም ትልቅ የነበረና በልዩ ዲዛይን የተሰራ ቤተ-ክርስትያን ሲመለከት ይህን ባለግርማ የነበረ ቤተ-ክርስትያን ማን ሰራው በማለት በአእምሮው ለሚፈጥረው ጥያቄ መልስ ይሰጠዋል፡፡ ይኸውም ቤተ-ክርስትያኑ የተሰራው በወቅቱ በነበሩ ነገስታት ስለሆነ አስፈላጊ ግባቶችንም ሆነ ጌጣጌጦችን ለማሟላት እንዳልተቸገሩ ይገልጽለታል፡፡ እንደዚሁም በነገስታት የተሰራች ቤተ-ክርስትያን መሆኗን አውቆ ልዩ ክብር እንዲሰጣትና ከአደጋም ሊጠብቃት እንደሚገባ ያስገነዝቡታል፡፡

ሁለተኛው ደግሞ እዚህ ቦታ ላይ ለመስራት ለምን ፈለጉ፣ ለምን ሌላ ቦታ ላይ አልሰሩትም ለሚሉት ጥያቄዎች  የሚሰጥው መልስ ነው፡፡ ይህም ማህበረሰቡ በእምነት ከሚቀበለውና በሐይማኖቱ ከሚሰበክለት ነገር ጋር ይገናኛል፡፡ ይኸውም በክርስትና ሐይማኖት የበቁ አባቶች እግዚአብሄር በራይ ተገልጦ እንደሚያናግራቸውና ፍላጎቱን እንደሚገልጽላቸው ይታመናል፡፡ በዚህም ምክንያት አብርሃ እና አጽበሃ እንዲሁም አቡነ ሰላማ በእግዚአብሄር የተመረጡና የተወደዱ ስለሆኑ በእራይ ተገልጦ ቤተ- ክርስትይኑ እንዲሰራ የፈለገበትን ቦታ አሳያቸው፡፡ ስራቸውን በማገዝ ቀን ሲሰራ የዋለው ቤተ-ክርስትያን ማታ ሁለት እጥፍ አድጎ እያደረ በሰዎች ብቻ ሳይሆን እግዚአብሄርም ተጨምሮበት በጣም ትልቅ ሆኖ ተሰራ በማለት ይተርካል፡፡ ይህን ታሪክ የሚሰማው ማህበረሰብም ቤተ-ክርስትያኑ እዛ ቦታ ላይ የተሰራው በእግዚአብሄር ፍላጎትና እርዳታ መሆኑን አውቆ ቦታው እና ቤተ-ክርስትያኑ በእግዚአብሄር የተመረጠና የተቀደሰ መሆኑን ተቀብለው ከበረከቱ ተካፋይ ለመሆን እንዲነሳሳ እና ለቤተ-ክርስትያኗ ልዩ አምልኮ እንዲያደርግ ያሳምነዋል፡፡

### 3.2. የገዳሟን ህልውና ለማስጠበቅ የሚነገሩ አፈ-ታሪኮችና ፋይዳቸው

አፈ-ታሪክ የሚነገረው‹‹አድማጩን ለማስተማር፣ለማስጠንቀቅ፣ለመምከር፣ ለመርዳት፣ ለማንቃት፣መረጃ ለመስጠት እንዲሁም አንድ ለተፈጸመ ታሪክ በቂ ገለጻና ማብራሪያ ለመስጠት ነው፡፡ ››(ሰለሞን 2007 ዓ.ም፣94)

በዚህ ጥናት የተሰበሰቡ አፈ-ታሪኮችም የገዳሟን ታሪካዊነት ለማስጠበቅና ገዳሟን እስከ መጨረሻው ለመትከል፣ ገዳሟን በክፉ የሚያስቧትን ለማስጠንቀቅ፣ ማህበረሰቡ ገዳሟ በአካባቢው ካሉ ቤተ-ክርስትያናት ቀድማ የተቆረቆረች መሆኖን በመግለጽ የቦታዋን ቅድምና አውቆና ተረድቶ እንዲጠብቃት፣ እንዲንከባከባት ያነሳሳሉ፡፡ እንዲሁም ምዕመናን አደጋ ሲመጣ ተግተው ሊፀልዩ እንደሚገባ እንዳይፈሩና ገዳሟን ለጠላት አሳልፈው እንዳይሰጡ ይመክራሉ፡፡ በተጨማሪም ማህበረሰቡ ከማንኛውም ጥቃት ድንግል ማርያም እንደምትታደገው በማመን እምነቱን፣ ቅርሱን መጠበቅ እንደሚገባው ፣ በያዘው ነገር ላይ መታመን  እንዳለበት ባይታመን አደጋ ሊገጥመው እንደሚችል የሚያስጠነቅቁ ናቸው፡፡ ለምሳሌ፡- የገዳሟን ጥንታዊነት ለማጉላት የተነገረን አፈ-ታሪክ እንመልከት፡-

> *በመርጡለ ማርያም አካባቢ ለመጀመሪያ ጊዜ የሰፈሩት የኩሽ ነገዶች ሲሆኑ ከክርስቶስ ልደት በፊት ከ2ኛው ሺ አመት ጀምሮ ለአንድ ሺ ሰባት መቶ አርባ ዓመታት ያህል በቦታዋ ሰፍረው እግዚአብሄርን በህገ ልቦና እያመሰገኑ ያለምንም ችግር በሰላም ስለኖሩ አገሯን ሃገረ ሰላም ብለው ሰይመዋት ነበር* (ቃ.መ፣ አያልነህ ፣ 2012 ዓ/ም)፡፡

ይህ አፈ-ታሪክ ለቤተ-ክርስትያኗ ህልውና ምን የሚሰጠው ጥቅም አለ በምንልበት ጊዜ የአካባቢውን ጥንታዊ ታሪክ በማሳየት ያኔም ቢሆን ይኖሩ የነበሩ የቦታዋ ነዋሪዎች ማንም ስለእግዚአብሄር ሳይገልጽላቸው በተፈጥሯቸው እግዚአብሄርን የሚያውቁ የተባረኩ ሰዎች ይኖሩበት የነበረ አካባቢ እንደነበር ያስገነዝባቸዋል። ስለዚህ ይህ ቦታ አስቀድሞም የተመረጠ ስለሆነ ሊጠበቅ ይገባዋል የሚለውን እንዲያስቡ ያደርጋቸዋል ።

ሌላው አፈ ታሪክ የኢትዮጵያን ቤተ-ክርስትያናት ለማውደም በ1530 ዎቹ ተነስቶ የነበረውን ግራኝ መሃመድን በሚመለከት የሚነገረው አፈ-ታሪክ ፋይዳ ነው።

> --- *ገዳሚ እስከ ዐፄ ልብነ ድንግል ልዩ እንክብካቤ ሲደረግላት ቆይቶ የግራኝ መሐመድ ወረራ ሆነ በዚሁ ዘመን ልብነ ድንግል እንደ ሞተ ልጁ ገላውዴዎስ ነግሶ ከግራኝ ጋር ለመዋጋት ሠልፍ አድርጎ ሳለ በእናቱ በሰብለ ወንጌል ምክር ጥር 21 ቀን 1535 ዓ.ም. መርጡለ ማርያም መጥቶ ብጻት (ስለት) ገባ። ብጻቱም የግራኝ መሐመድን ድል ያሳየሸኝ እንደሆነ የክብር ልብሴን እሠጣለሁ ብሎ ተስሎ እንደተመለሰ ፎገራ ዘንተራ ከተባለው ቦታ ጦርነት ተደርጎ የካቲት 26 ቀን 1535 ዓ.ም. ግራኝ መሐመድ በጥይት ሞተ። አፄ ገላውዲወስም በስለቱ መሰረት የግራኝ መሐመድን የክብር ልብስ የራሱን ቀሚስና የብራና ዳዊት ለመርጡለ ማርያም ሰጠ* (*ቃ.መ፣* ዘላለም ፣ 2012 ዓ/ም)።

ይህ አፈ-ታሪክ ቤተ-ክርስትያኗ ላይ ጥቃት ለማድረስ የሚሞክሩ ወገኖችን ማህበረሰቡ ማርያም እንደምትረዳቸው አምኖ እና በስራው እንደምትደሰት አውቆ የገላውዲዎስን አርአያ ተከትሎ ከጥቃት እንዲከላከላት የማበረታታት ሚናን ይጫወታል። በተጨማሪም ሊያጠቋት የሚፈልጉ አካላት ካሉም ለቤተ-ክርስትያኗ ደህንነት የሚዋጉ አካላትን ማርያም ስለምታግዛቸው ከሽንፈት እንደማያመልጡ እና እራሳቸው እንደሚጠፉ ያስጠነቅቃቸዋል።

ቀጥሎ የቀረበውን አፈታሪክ ደግሞ እንመልከት ፡-

> *ከገዳሚ በስተ ደቡብ ቡርቃ ከሚባለው ስፍራ ፀበል ቦታ ነበር። የአካባቢው ማኅበረሰብ እንደማንኛውም ውሃ ይገለገሉበት ነበር፡ ከእለታት አንድ ቀን አንድ የጤና ችግር ያለበት ሰውነቱ አብጦና ተነፍቶ በህክምናና በፀበል ብዙ ደክሞ ፈውስ አጥቶ ይኖር ነበር። በህልም እዚህ ቦታ ቢጠመቅ እንደሚድን ይመለከታል። ከቦታውም በብዙ ድካም ደርሶ ሲመለከት ሰዎች ሲዋኙና ሲታጠቡበት ያያል በዚህ ጊዜ ከቦታው እንዳልደረሰ በማሰብ አዝኖ ሊመለስ ይወስናል። ደክሞት ስለነበር የተደሞ እንቅልፍ ተኛ በራዕይም እንዳትመለስ ግባና ተጠመቅ ፀበሉንም ጠጣ ሲል ያሳየዋል። ከእንቅልፍ ሲነቃ ያየውን ራዕይ እያሰላሰለ ከፀበሉ ገብቶ ተጠመቀ፤ ፀበሉንም ጠጣ፤ በዚህ ጊዜ ሆዱን እየነፋና ሰውነቱን እያሳበጠ ከሚያሰቃየው በሽታ ተፈወሰ ይህ ሰው ለበሽታው ፈውስ አጥቶ ሲሰቃይና ተስፋ ቆርጦ በነበረበት ሰዓት ሲጠመቅ ያገኘውን ድኅነት ምስክርነት በመስጠቱ የሰሙና የተመለከቱ ሰዎች የፈለቀው ፀበል መሆኑን ተረድተው በጸበልነቱ እንዲከበርና ዙሪያው እንዲታጠር ተደርጓል። በርካታ ህሙማን ፈውስ ሳጡለት ህመማቸው ፈውስ በማግኘት ወደቤታቸው ይሄዳሉ (ቃ.መ፣ አያና ፣ 2012 ዓ/ም)።*

ከላይ ከቀረበው አፈ ታሪክ ለመረዳት እንደሚቻለው ያልተከበረ ሊከበር የሚገባ ሥፍራ ላይ ውሃ እንደነበር ይገልጻል፤ ይህ ውሃ ማንኛውም የማህበረሰቡ አባል ሲጠቀምበት እንደነበርም

ያሳያል፤ የቦታው ህልውና እንዲከበር በአፈ ታሪኩ ያስተምርበታል፡፡ ይኸውም በህክምናም ሆነ በፀበል ፈውስ ያጣ ህመምተኛ በተጠቀሰው ቦታ ቢጠመቅ እንደሚድን ህልምና ራዕይ ያሳየዋል፤ በተግባርም ይጠመቃል፤ ተጠምቆም ይድናል፡፡ በመሆኑም ለቦታው መከበር ዋናው ምክንያት መድሀኒት የታጣለት በሽታ ፈውስ ማግኘቱ ሆኖ እናገኛለን፡፡ ይህን የሚሰሙ የማህበረሰቡ አባላት በቀጣይም የቦታው ክብር ተጠብቆ እንዲኖር እንዲያደርጉ የመትከል ሚና አፈ ታሪኩ ይጫወታል፡፡ በተግባር ፈውስ የታየበት መሆኑ ስለሚተረክም ማህበረሰቡ አምኖ አሁን ድረስ ይንከባከበዋል፤ ይጠብቀዋል፡፡ አፈ ታሪኩ የቦታውን ቅድስና በማስጠበቅ በኩል ያለው ሚናም ከፍተኛ ነው፡፡

> *በእነማይ ወረዳ የሚገኘው ዲማ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን በትክል ከመርጡ ለማርያም ገዳም ይቀድማል ብለው ከመርጡ ለማርያም ጋር ይወዛገቡ እንደነበርና ውዝግቡም ደብረ ዲማ ቅዱስ ጊዮርጊስ ወይም ዲሞች እኛ እንቀድማለን በማለት አንስተውት በነበረው ክርክር መርጡ ለማርያምን ወክለው ሲከራከሩ የነበሩት ፊታውራሪ እንድሬ ዲማ ከመርጡለ ማርያም ይቀድማል መባሉ እንኳንስ መብለጡ መስተካከሉ አለን፤ የሰማይቱ ቅዱስ ጊዮርጊስ በረከቱ ይድረሰንና ዲማ በትክል መርጡ ለማርያምን እንኳን ሊቀድም መርጡ ለማርያም ስትተከል የሰማይቱ ቅዱስ ጊዮርጊስ አባ ዞሮንቶስ አልተወለደም ብለው አስደናቂ መልስ በመስጠታቸው ዲሞች ምላሽ አጥተው በዝምታ አልፈውታል ይባላል (ኃይለ ኢየሱስ ፣ 2013 ዓ.ም)፡፡*

ከአፈ ታሪኩ ለመረዳት እንደሚቻለው የቦታ ቀዳሚነት ጉዳይ በተለያዩ ደብሮችና ገዳማት መካከል ክርክር እንደነበር ነው፡፡ የቦታዋን ቅድምና ለማረጋገጥ ማህበረሰቡ ተከራካሪው አካል አምኖ በተቀበለው ነገር ላይ ተመስርቶ ምላሽ ሲሰጥ እንመለከታለን፤ ይህ አፈ ታሪክ ደግሞ አሁንም በተለያዩ አጋጣሚዎች ለማስተማሪያነት ያገለግላል፡፡ ምዕመኑ የቦታዋን ቅድምና አውቆና ተረድቶ እንዲጠብቃት፣ እንዲንከባከባት ያነሳሳል፡፡ የያዘው ነገርም ከሌሎች የበለጠ መሆኑን በማስገንዘብ የገዳሟ ታሪካዊነትና ክብር ተጠብቆ እንዲቆይ በቀጣዩም ትውልድ ተስተላልፎው እንዲቀጥል የማድረግ ፋይዳ እንዳለው ከአፈ ታሪኩ መረዳት ይቻላል፡፡ በመሆኑም አፈ ታሪኩ የመጠበቅ የማስጠበቅ ፋይዳ አለው፡፡

> *… የደርግ መንግስት ይዞት የመጣውን ሀይማኖት አልባ ሥርዓት የጎጃም ህዝብ አልቀበል ብሎ አምፆ ስለነበር ይህን አመጽ ለመቆጣጠር ያሰማራው ወታደር ወደ መርጡለ ማርም ታሪካዊ ቦታ ደረሰ፡፡ መልእክተኞቹ ህዝቡ ጦሩን በሰላም እንዲቀበል የማረጋጋት ስራ በመስራታቸው ህዝቡ ጦሩን በሰላም ተቀብሎ ወደየቤቱ ገባ መልእክተኞቹ ግን ለሊቱን የከተማውን ህዝብ ከዘረፉ በኋላ ወደ ገዳሟ በመምጣት በቤተ መዘክር ያገኟቸውን ካህናት በስውር የተቀመጡ ቅርሶችን እንዲያሳዩዋቸው ከፍተኛ ስቃይ ሲያሳዩዋቸው ካህናቱም ከሚታዩት ቅርሶች ውጭ ያሉትን ይዘው እንደሸሹ የተመደቡት ካህናት ወዴት እንደወሰዱት አናውቅም እኛም እዚህ ያለውን*

*ቅርስ እንድንጠብቅ ስለተመደብን ነው እዚህ የተገኘነው ብለው ቅርሱ ያለበትን እንደማያውቁ ገለጹላቸው፡፡ ወደ ገዳሚ ቤተ መዘክር ዘልቀው በመግባት የብራና መጻህፍቶችን ፣የነገስታት የወርቅ የራስ ቁሮችን፣ በርካታ ቅርሶች ዘርፈው ጭነው ወሰዱ፤ ለሊት በዘረፋ ሰአት ወደገዳሚ የተጠለሉ ክርስቲያኖችን በስላሴ ቤተክርስቲያን በማስገባት በሦስቱ በር መትረየስ ጠምደው ትእዛዝ ይጠባበቁ ነበር፡፡ መትረየስ የተጠመደባቸውን ክርስቲያኖች የአምላክ እናት ቅድስት ድንግል ማርያም ከዚህ ጭንቅ ታድናለች በፍጹም እምነት ድረሽልን እያላችሁ ፀልዩ ሲሉ አባቶች አዘዙ፤ በጸሎትም ተጉ አዛዡም ትእዛዝ እንዲተኩሱ ሲሰጥ ተኳሾች የሳቡት ምላጭ ግዳጃቸውን ሊወጡ አልቻሉም፤ ወደሰማይ ሲሞክሩ የቤተክርስቲያኑን ታዛ ጣራና መስኮቱን በጣጠሰው ዳግመኛ ወደሰዎቹ አነጣጥረው ምላጭ ሲስቡ ክንዳቸው በመዛሉ ከአቅማቸው በላይ መሆኑን ተናገሩ፤ አዛዡም በብስጭት ተኳሹን ልቀቅ ብሎ ገፍትሮ ካህናቱ ባሉበት በር የተጠመደውን መትረየስ ተቀብሎ በርከክ ብሎ ምላጭ ሲረግጥ በጦር እንደተወጋ ድምጽ አሰምቶ የኋሊት ተፈነገለ፤ ሲወድቅ አለቃቸውን ተሸክመው በቦታው ላይ በፈጸሙት ግፍ የእመቤታችን ቁጣ መሆኑን ተረድተው ጓዛቸውን ሰትረው ሲመለሱ የታፈኑት ክርስቲያኖች በድንግል ማርያም አማላጅነት የአንድም ሰው ሕይወት ሳይጠፋ ከእልቂቱ ሊተርፉ ችለዋል(ቃ.መ፣ ተፈሪ ፣ 2012 ዓ/ም)፡፡*

በዚህ አፈ ታሪክ ከተነሱ ነጥቦች መካከል የደርግ ባለ ስልጣን መልእክተኞች የጭካኔ ተግባር አንዱ ነው፡፡ በክርስትናው ፀንቶ የሚኖረውን የጎጃም ህዝብ ንብረቱን ከወረሱ በኋላ በዘረፋው ተሰቅቆ ወደ ቤተክርስቲያን ቢገባም ተከትለው የግድያ ሙከራ እንዳደረጉበት ይተርክልናል፤ ነገር ግን ምዕመኑ ከአባቶች የተላለፈውን መልእክት ትዕዛዝ መሠረት በማድረግ ማለትም ‹‹የአምላክ እናት ቅድስት ድንግል ማርያም ከዚህ ጭንቅ ታድናለች በፍጹም እምነት ድረሽልን እያላችሁ ፀልዩ›› የሚለውን በመቀበል አባቶች ባዘዟቸው መሠረት በጸሎትም ተጉ አዛዡም እንዲተኩሱ ትዕዛዝ ቢሰጥም ተኳሾች የሳቡት ምላጭ ግዳጃቸውን ሊወጡ አልቻሉም፤ የባሰውን አዛዡ ሳይቀር እንደከሸፈበት ያሳያል፡፡

በአፈ ታሪኩ አንድም ምእመናኑ የአባቶቹን ትዕዛዝ መቀበል እንደሚገባቸው፤ የእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምን አዳኝነት ያሳያል፡፡ አንድም በገዳሚ የሚገኙ ቅርሶችን ለመዝረፍ የሚመጡ ጨካኞች ፍጻሜያቸው እንደማያምር ፤ የገዳሚን ምዕመናን የሚተናኮሉትን እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም እንደምትታደጋቸው አደጋ ሲመጣ ተግተው ሊፀልዩ እንደሚገባ ያስተምርበታል፡፡ በአንጻሩ ደግሞ ጨካኞች፣ እኩዮች ከእኩይ ድርጊታቸው እንዲታቀቡ የማስጠንቀቅ ተግባር ሚና አፈ ታሪኩ እንዳለው ያሳያል፡፡

ከዚሁ አፈ ታሪክ ጋር ተያይዞ የሚነገረው ታሪክ የሚከተለው ነው፤

*በደርግ ዘመን የመጡ መልእክተኞች የዘረፏቸውን በካምፓቸው ወስደው ስጋጃውን አንጥፈው ሲተኙበት በልዩ ልዩ ደዌ እየታመሙ ጤና በማጣታቸው የስጋጃ ምንጣፉን*

*ወደገዳሟ ተመልሶ እንዲገባ ሲያደርጉ ከህመማቸው ድነዋል። ሌሎቹን ቅርሶች በኢሊኮፍተር ጭነው ለመውሰድ በረራ ሊያደረጉ ሲሞክሩ ሞተሩ አልነሳ ስላለ ተደናግጠው ሲያሰላስሉ በስጋጃ ምንጣፏ ሲተኙ ያጋጠማቸውን የጤና ችግር አስታውሰው ሹሞቹ ከቤተክርስቲያን የመጣ ንብረት ከውስጥ ገብቶ እንደሆነ ፈትሹ የሚል ሀሳብ ተነስቶ የገዳሟን ቅርሶች ከውስጥ አውጥተው ሲሞክሩ ሞተሩ ተንቀሳቀሰ፤ በዚህ ጊዜ ካህናቱን አስጠርተው ፀሎት አድርጉልን በስህተት አምጥተነው የነበረው የገዳሟ ቅርስ ይኸውላቸሁ ተቀበሉን ብለው ለከህናቱ አስረክበው ካህናቱም ቅርሳቸውን በምስጋና ተቀብለው እግዚአብሔርን እያመሰገኑ ከቤተመዘክሩ ቅርሱ በክብር እንዲቀመጥ አድርገዋል። ከዚያ ለማብረር ሙከራ ሲደረግ ኢሊኮፍተሩ ጤናማ አገልግሎቱን መስጠት ጀመረ (ቃ.መ፣ ጥሉመ ልሳን ፣ 2012 ዓ/ም)።*

ይህ አፈ ታሪክ እንደሚያሳየው ገዳሟን የሚደፍሩ የገዳሟን ቅርሶች የሚዘርፉ ሰዎች መጥፎ ነገር እንደሚገጥማቸው፣ እንደማይቀናቸው እንደማይሳካላቸው ነው። ድንግል ማርያም በካህናቱና በክርስቲያኖች ላይ ሊፈፀም የነበረውን ጭካኔ የተሞላበት ጭፍጨፋ እንዳያገኛቸው በልዩ ተዓምር ከማዳኗ በተጨማሪ ቅርሷንም በልዩ ተዓምር እንደምትታደግ ቅርሷን የሚጠብቁትን እንደምትጠብቃቸው ያመለክታል። አፈ ታሪኩ የማጠንከር/የመትከል ተግባር እንዳለው ያሳያል፤ ማህበረሰቡ ከማንኛውም ጥቃት ድንግል ማርያም እንደምትታደገው በማመን እምነቱን ቅርሱን መጠበቅ እንደሚገባው በተጨማሪ ማህበረሰቡ በያዘው ነገር ላይ መታመን እንደሚገባ ባይታመን አደጋ ሊገጥመው እንደሚችል ያስጠነቅቃል።

*የግራኝ መሀመድ ወረራ ጊዜ አጼ ልብነ ድንግል እንደሞቱ ልጃቸው ገላውዲዎስ ነግሶ ሳለ የአጼ ገላውዲዎስ ቀራቢ የነበሩት ‹‹ግራኝን ሊወጉ አስበው ከሆነ እባክዎን ቅድሚያ ፋሲካን አብረን በሰላም እንዋልና በኋላ ይዋጋሉ›› በማለት በፍጹም እምነትና ቆራጥነት ከግራኝ ጋር ለመዋጋት ሰልፍ አደረገ፤ እናቱ ሠብለ ወንጌልም ግራኝ ድል እንዲሆንላቸው ከጎንደር ተነስተው ጥር 21 ቀን 1535 ዓ.ም መርጡለ ማርያም መጥተው ብጽዓት ገቡ። ብጽዓቱ ‹‹የግራኝ መሀመድን ሽንፈት ያሳየሽኝ እንደሆነ የልጄን የገላውዴዎስን የክብር ልብስና የእኔን የክብር ልብስ እሰጣለሁ›› ብለው እንደተመለሱ ጎንደር ውስጥ ደንቢያ ዘንተር ከተባለው ተራራ ስር ጦርነት ተደረገ፤ ንጉሱም ምልጃ ተማጽኖ ቁርባንን ተቀበለ። በዕለተ ረቡዕ ከቀኑ በ 3 ሰዓት የካቲት 27 ቀን 1535 ዓ.ም ግራኝ መሀመድ በጥይት ተመትቶ ሞተ። የሞተበት ቦታ እስከአሁን ድረስ ‹‹ግራኝ በር›› እየተባለ ይጠራል። አጼ ገላውዲዎስም በእናታቸው ብጽዓት መሰረት የግራኝ መሀመድን የክብር ልብስና ቀሚስ የእናቱንና የራሱን የክብር ልብስ እንዲሁም የብራና ዳዊት አድርጎ ለመርጡለ ማርያም በብጽዓቱ መሰረት ሰጠ። በዚህም መሰረት በእመቤታችን ኃይል ግራኝ ድል ስለተመታና ሰራዊቱ ስለተማረከ ‹‹የግራኝ እመቤት›› እየተባለች እስከአሁን ድረስ ትጠራለች።* (ምትኩ፣1995 ዓ/ም)

ከላይ ከቀረበው አፈ ታሪክ ለመረዳት እንደሚቻለው መርጡለ ማርያም ከአካባቢዋ ርቀው የሚገኙ ምዕመናን የሚማፀኗት ስለት የሚገቡባትና ከጠላት ጋር በሚደረግ ፍልሚያ ድል የምታጎናጽፍ እንደሆነች ያሳያል። በአሁኑ ዘመን የሚገኙ ምዕመናን በገዳሟ ላይ በሚፈፀም ወረራና ዘረፋ ከጠላቷ ጋር ፊት ለፊት እንዲፋለሙ ያበረታታል። ቀጥሎ የቀረበው አፈ ታሪክም በገዳሟ የማርያም ኃይልና ብርታት በምእመኗ ላይ እንደሚኖር የሚጠቁም ነው።

*ንጉስ ተክለሃይማኖት ጎጃምን ያስተዳድሩ በነበረበት ወቅት ከቡሬ ዳሞት የመጣ የአካባቢውን ህዝብ ይዘርፍና በሽፍትነትም ይኖር የነበረ ፊታውራሪ ጓንጉል የሚባል ሰው መርጡለ ማርያም ብዙ ሀብትና ንብረት አላት ሲባል ይሰማ ስለነበር በተለምዶ ቦቂት እየተባለ የሚጠራውን ሰራዊቱን ይዞ ሊዘርፍ ሲመጣ ቀደም ሲል በንጉስ ምኒልክና በንጉስ ተክለሃይማኖት መካከል በ1874 ዓ.ም ሚያዚያ 30 ቀን እምባቦ ላይ በተደረገው ጦርነት እንደተካፈሉ የሚነገርላቸውና በጊዜው የእነሴና የእነብሴው ገዥ የነበሩት ደጅ አዝማች ወዳጄ ለዘረፋ እንደመጣ አውቀውና ተረድተው ህዝቡን በማስተባበር ፊታውራሪ ጓንጉልን ሊገጥሙት ባሰቡ ጊዜ እመቤታችን በራዕይ ተገልጻ ‹‹ወዳጄ አይዞህ እረዳሀለሁ›› ብላ ስለነገረቻቸው እመቤታችንን ኃይልና ምርኩ አድርገው ገጥመው እንዳሸነፉትና በዚህም ምክንያት ‹‹የጓንጉል እመቤት›› ተብላም ትጠራለች፡፡ (ቃ.መ፣ ዘውዱ ፣ 2012 ዓ/ም)፡፡*

ከላይ በአፈ ታሪኩ እንደተገለፀው የመርጡለ ማርያምን ሀብት ንብረት ለመዝረፍ የሚመጡ ሽፍቶች በድንግል ማርያም ኃይል ድል እንደሚደረጉ ያሳያል፤ በተጨማሪ ገዳሚን ለመዝረፍ የሚያስቡ እንዲታቀቡ ያስጠነቅቃል፡፡ ምእመኑም ኃይልና ብርታትነቷን በመተማመን ድል ከሱ ጋር እንዳለች በማመን ለገዳሚ ህልውና መጠበቅ የኩሉን ድርሻ እንዲወጣ ያበረታታበታል፡፡

## 4.ማጠቃለያና አስተያየት

### 4.1. ማጠቃለያ

ይህ ጥናት በርዕሰ ጉዳዩ ላይ ለማጥናት ባለን ፍላጎትና ከክለሳ ድርሳናት ለመረዳት እንደተቻለው ርዕሰ ጉዳዩ ያልተጠና በመሆኑ የተደረገ ነው፡፡ የጥናቱ ዋና አላማም ከመርጡለ ማርያም ገዳም ጋር ተያይዘው የሚነገሩ አፈ-ታሪኮች የገዳሚን ህልውና በመጠበቅ ያላቸው ፋይዳ ምን እንደሆነ መመርመርና መተንተን ነበር፡፡ በመሆኑም ለጥናቱ አስፈላጊ መረጃዎች በቃለ መጠይቅና በተተኳሪ ቡድን ውይይት ተሰብስበዋል፡፡ ጥናቱ አይነታዊ ጥናት እንደመሆኑ የተሰበሰቡ መረጃዎች በገላጭ ተንታኝ መንገድ ቀርበዋል፡፡ ለመረጃ መተንተኛነት ከፎክሎር መረጃ መተንተኛ ንድፈ ሃሳቦች መካከል ተግባራዊ /ፋይዳዊ ንድፈ ሃሳብ አገልግሎት ላይ ውሏል፡፡

ተግባራዊ ንድፈ ሃሳብ የፎክሎሩን ጥቅም መተንተን ላይ ያተኩራል፤ ከትንታኔው ለመረዳት እንደተቻለውም፡-

በመርጡለ ማርያም ገዳም ዙሪያ የሚነገሩ አፈ-ታሪኮችን ታሪክ ማህበረሰቡ አምኖ እንዲቀበል እግዚአብሄር፣ ማርያም፣ የኢትዮጵያ የቀድሞ ነገስታት (ቀዳማዊ ምኒሊክ፣ አብረሃ ወ አጽብሃ፣ አጼ ገላውዲዎስ) እና በአካባቢው የሚታወቁ የቦታ ስያሜዎች ይጠቀሳሉ፡፡ የእነሱ መጠቀስ ደግሞ ማህበረሰቡ ቅርሱን እንዲጠብቅ የማበረታታት ጉልበቱ ከፍተኛ እንደሚያደርገው ተስተውሏል፡፡

እንዲሁም በታሪካዊቷ መርጡለ ማርያም ገዳም ዙሪያ የሚነገሩ አፈ ታሪኮች በገዳሟ እና በማህበረሰቡ አባላት ላይ የሚፈፀሙና የተፈፀሙ ጥቃቶች በድንግል ማርያም ልዩ ተዓምር መክሸፉን ያሳያሉ፤ ይህም ማህበረሰቡ በገዳሟ ዙሪያ ለሚገጥሙ ጥቃቶች ድንግል ማርያምን ተስፋ አድርጎ ፊት ለፊት ሊጋፈጥ እንደሚገባ ይጠቁማል። እንዲሁም ገዳሟን ሊያጠቋት የሚሞክሩ ጠላቶችም እንደማይሳካላቸውና እንደሚዋረዱ ያስጠነቅቃቸዋል። በተጨማሪ በገዳሟ የሚፈፀሙ ዘረፋዎችን የማህበረሰቡ አባላት ሊመክቱ እንደሚገባ፤ ምዕመናን ለአባቶች ሊታዘዙ እንደሚገባ፤ የጸበሏን ፈዋሽነትና ታሪካዊነቷን በማጉላት ቦታዋ እንድትተከልና እንድትከበር የማድረግ ተግባር አላቸው፤

በአጠቃላይ አፈ - ታሪኮቹ ከምእመኑ፣ ከቅርሶች፣ ከማህበረሰቡ፣ ከቦታዋ አንጻር የሚነገሩ መሆናቸውንና የገዳሟን ህልውና ለማስጠበቅ ያላቸው ፋይዳ ከፍተኛ መሆኑ ለመረዳት ተችሏል።

## 4.2. አስተያየት

ከዚህ ጥናት ውጤት መረዳት እንደሚቻለው አፈ-ታሪኮች ህዝቡ የአገሩን እና የአካባቢውን ቅርስ እንዲጠብቅና ለቀጣይ ትውልድ እንዲያስተላልፍ ለማድረግ የሚጫወቱት ሚና ከፍተኛ እንደሆነ ነው። የቤተክርስቲያን አባቶች ገዳማትንና በገዳማት የሚገኙ ቅርሶችን፣ ሀብቶችን ለመጠበቅ ከሚጠቀሙባቸው ጥበቦች አንዱ አፈ-ታሪክ እንደሆነ ያሳያል። በአፈ-ታሪኮች ላይ ጥናት ማድረግና ፋይዳቸውን መጠቆም ደግሞ ከምሁራን የሚጠበቅ ቢሆንም ትኩረት ግን ተነፍገዋል። በመሆኑም እንደዚህ ያሉ አፈ ታሪኮች እየተሰበሰቡ ሊጠኑና ትኩረት ሊሰጡ ይገባል እንላለን።

### ዋቢዎች


ምትኩ ደምሴ። **መርጡለ ማርያምና ታሪኳ።** ዳሽን ማተሚያ ቤት። አዲስ አበባ፣1995 ዓ.ም።

ኃይለ ኢየሱስ ገብረ ማርያም። **የጥንታዊትና ታሪካዊት መርጡለ ማርያም ገዳም**

**ታሪክ በአጭሩ።** 2010 ዓ/ም፣ ማተሚያ ቤቱ ያልተጠቀሰ።

ሰሎሞን ተሾመ። **ፎክሎር ምንነቱና የጥናቱ የትኩረት አቅጣጫ።**ፋር ኢስት ኃ/የተ/የግ/ማህበር፣

አዲስ አበባ2007 ዓ.ም፡፡

ዘሪሁን አስፋው፡፡ **የሥነ ጽሑፍ መሠረታውያን**፡፡ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፣አዲስ አበባ፣ 1992 ዓ.ም፡፡

ፈቃደ አዘዘ፡፡ **የሥነ-ቃል መምሪያ**፡፡ ኢንተርናሽናል ጀርመናዊ የጎልማሶች ትምህርት መርጃ ተቋም፣ አዲስ አበባ፣ 1991 ዓ/ም፡፡

Bascom, William R.**Four Functions of Folklore.** The Journal of American Folklore, Vol.67, No.266, 1954.

Degh, Linda. "Folk Narrative**."** In Richard Dorson (Ed) **Folklore and Folklife An Introduction.**The university of Chicago Press. Chicago and London. 1972. P.72-77

Green,A. Thomas (ed.). **An Encyclopidia of Beliefs, Customs, Tales, music and Art.** Santa Barbara, California ,denver: ABC- CLIO,Inc. 1997.

Okpewho, Isidore. **African Oral Literature. Back Grounds, Character and Continuity**. Indianapolis: Indiana University Press, 1992**.**

Paul B.Henze. **The Monastry of Mertule Maryam in Gojjam.** A major medival Ethiopian Architectural Monument: Warszawa. .1919.

***Sims*** C**.**Martha and Martine ***Stephens***. *Living Folklore***: An Introduction to the Study of People and Their Traditions**. ***Logan,Utah: Utah state university.*** 2005.